ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎችን ያጠቃልላል ስለዚህ እነዚህን ተግባራት መስራት ይቻላል ይላሉ። አላሁ አዕለም

### 4. ፆም

“አላህ ሆይ የሻእባንን ወር እንዳደርስከን ሁሉ የርመዳንን ወርም አድርሰን”

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ በናንተ ላይ ጾም ግዳጅ ሆኖ ተጻፈባችሁ በነዛ ከናንተ በስተፊት በነበሩት ሕዝቦች ላይ እንድተጻፈባችው ሁላ አላህን ልትጠነቀቁት ይከጅላልና” (አል-በቀራ፣ 183)

ጾም ማለት በቋንቋ ደርጃ መታቀብ የሚለውን ፍች ይሰጠናል። ወደ ሸሪአዊ ትርጉሙ ደሞ ሰንወስደው ከጎህ መቀደድ ጀምሮ እስከ ፀሃይ መጥልቅ ድርስ ባለው ጊዜ ከምግብ፤ ከመጥጥ፤ከግብር ስጋ ግንኙነት መታቀብ ማለት ነው። በተጨማሪም አላህ(ሰ.ወ) ከከለከላቸው ነገሮች ሁሉ መታቀብን ያጠቃልላል።በርመዳን ወር ካሉ ቱርፋቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡ የጀነት በሮች መከፈት፤ የጀሀነም በሮች መዘጋት፤ የሰይጣን መታሰር፤ የመልካም ሰራ አጅር እጥፍ ድርብ ሆኖ መከፈል ናቸው።ታድያ እንድዚህን እና ሊሎችም በርካታ ትሩፋቶችን ይዞልን የሚመጣውን ወር እንዲት መቀበል አለብን? ይህንን አመታዊ እንግዳ ለመቀበል ከመቸውም በላይ በበለጠና በጠነከር መልኩ በአካልም ሆነ በመንፍስ ዝግጅት ማድረግ ከኛ ይጠበቃል። ምክንያቱም ይህ ወር ቁርአን የወርደበት፤ በውስጡ ከሺ ወር በላይ የሆነች ወሳኝቱን ለሊት(ለይለተል-ቀድር) መያዙ፤ የመላኢካዎች እስቲግፋር፤ በተጨማሪም ቸልተኞች የሚቀሰቀሱበት ፤ ሃጢያተኞች የሚፅፀቱበት፤ የጠመሙት የሚቃኑበት፤ የአላህ (ሱ.ወ) ፅጋና ምህርት ለባሮቹ ከመቸውም በላይ ከፍ የሚልበት ወር ስለሆነ ነው።

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ.) ረመዳን ካሉት ፊዳኢሎችና በረከቶች ዋና ዋናዎቹን በሚጠቅሱበት ሐዲሳችው ውስጥ እንዲህ ይላሉ “መጀመሪያው እዝነት፤ መካከለኛው ምህረት፤ መጨረሻው ደግሞ ከእሳት ነጻ የሚያወጣበት ነው።” ማለትም በመጀመሪያ አስር ቀናቶች አላህ (ሱ.ወ) ለትክክለኛ ባሮቹ እዝነቱን ያርከፈክፍባቸዋል፡ በሁለተኛው አስር ቀናቶች ደግሞ ምህርቱን ይለግሳቸዋል፡ በመጨርሻም አስርት ቀናት እነዛን ጿሚዎች ከእሳት ነጻ የሚያወጣበት ይሆናል።ይህንን እና መሰል ትሩፋቶችን የምናገኘው የረመዳንን ወር ስላገኘን ብቻ ሳይሆን በረመዳን ወር የሚፈለግብንን ግደታ ከፈፀምንና መልካም ነገሮችን ካበዛን ይበረመዳን ወር በጣም ተወዳጅ የሆኑ አምልኮአዊ ተግባራቶች እንደሚከተሉት ይሆናሉ፦ ቁርአንን በብዛት ማንብብ፤የሱና ሰላቶችን ያለማሳለፍ፤ ፈርድ ሰላቶችን በወቅቱ መስገድ ፤ተራዊህ (የለሊት) ሰላቶችን መስገድ፤ ዱዐ እና ዚክሮችን በብዛት ማድርግ፤ ኡምራ ማድርግ፤ ሰደቃ መስጠት፤ ኢእቲካፍ ማድርግ ( መስጅድ ውስጥ መቀመጥ) ናቸው። በዚህ በተከበረውና በተቀደሰው ወር በተቻለን መጠን ከልክ ያለፈ ምግብ እና ያላስፈላጊ ነግሮችን በመስራት የኢባዳ ጊዜያችንን እንዳይሻማን ማድረግ አለብን። በመጨርሻው አስርት ቀናት ወገባችንን ታጥቀን በኢባዳ ላይ መበራታት ይኖርብናል። አላህ (ሱወ) ወንጀላቸውን ምሮላቸው ፣ በእዝነቱ አካቧቸው፤ በራህመቱ አዝኖላቸው፤ ከእሳት ነጻ ከሚወጡት ያደርገን። አሚን!

### 5. ሃጅ

ሀጅ ማለት የተከበረውን የአላህን ቤት በመጎብኘትና ግደታዊ የሆነውን አምልኮ በውስጡ ለመፈፀም የሚደረግ ጉዞ ነው። የሀጅ ጉዞ የመንገዱን ጣጣ በቻለ በእያንዳንዱ ሙስሊም በሀየሃጅ ሸርጠች፦ ሙስሊም መሆን፣ ለአቅመ አዳም(ሄዋን) መድረስ፣ ጤናማ መሆንና ከባርነት ነፃ መሆን ናቸው ሃጅ ዋና ዋና መስፈርቶች አሉት፡ ኢህራም ማድረግ፤ ጠዋፍ፤ ሰዕይ (መሮጥ)፤ ፀጉርን ማሳጠር (መላጨት)፤አረፋ ላይ መቆም እና መሰናበቻ ጠዋፍ ናቸው :: ሃጅ በርካታ አላማዎች አሉት :: በመጀመሪያ ሊጠቀስ የሚገባው የሙስሊሞችን አንድነትና አብሮነት የሚያሳይ መሆኑ ነው :: ሁሉም ሙስሊም አንድ አይነት ነጭ ጨርቅ ለብሶ ያለ ምንም ልዩነት ወደ አሏህ ቤት ሲያመራ መሪ ተመሪ ሃብታምድሃ ጥቁር ነጭ ሳይል ሁሉም በአንድ አይነት ገጽታ “አቤት ብያለሁ ጌታዬ ሆይ፣ አቤት ብያለሁ ጌታዬ ሆይ፣ አጋር የለህም አቤት ብያለሁ በእርግጥም ምስጋናም ጸጋም ለአንተው ነው፡ ሰልጣንም ለአንተ ነው፡ አጋር የለህም” በማለት ሀጃጁ እራሱን በማስተናነስ ታዛዥ መሆኑን ይናገራል ። “ሀጀል መብሩር ወሳዕየን መሽኩር ወዘንበር መግፊር “አላህ ያድርግልን፡ አሚን!

ወቢሏሂ ተውፊቅ




# አል-ኢስላም

በበድር ኢትዮጵያ የሴቶች ዳእዋ ግሩፕ ተዘጋጅቶ የቀረበ

Badr Ethiopia Sisters

# አምስቱ የእስልምና መሰረቶች

የእስልምና መሰረቶች አምስት ናቸው። እነዚህም እንደሚከተሉት ይሆናሉ። ሸሃዳ፡ ሰላት፡ ዘካት፡ ሃጅ እና ፆም ናቸው። ለዚህም ማስረጃው ፡ አብደላህ ኢብን ኡመር ኢብኑል ኸጣብ (ረ.ዓ.) ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ ብለዋል፡ “ እስልምና የተገነባው በአምስት ነገር ላይ ነው። ከ አላህ ሌላ የሚመለክ አምላክ የለም ሙሐመድም (ሰ.ዐ.ወ.) የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር ፣ ሰላትን መስገድ፣ ዘካትን መክፈል፣ ሃጅ ማድረግ እና የረመዳንን ወር መጾም ናቸው።” (ቡኻረና ሙስሊም ዘግበውታል)

ከዚህ በመቀጠል እነዚህን አምስቱን የእስልምና መሰረቶች በዝርዝር እናያለን።

## 1. ሸሃዳ

ሸሃዳ ዋነኛና ተቀዳሚ ከእስልምና መሰረቶች ሲሆን አንድን ሙስሊም ሙስሊም ሊያሰኘው የሚችለው “አሽሃዱ አን ላ ኢላሃ ኢለ አላህ ወ አነ ሙሐመድ ረሱሉላህ” ትርጉሙም “ከ አላህ ሌላ የሚመለክ አምላክ የለም ሙሐመድም (ሰ.ዐ.ወ.) የአላህ መልዕክተኛ ናቸው” የሚለውን ቃል ትርጉሙን በማወቅ በምላስ መናገር እና እውነታውን በልብ አረጋግጦ በመቀበል ሲተገብር ነው።

ላ ኢላሃ ኢለ አላህ የሚለው ቃል ሁለት መሰረቶች (አርካን) አሉት። አንደኛው “ላ ኢላሃ” ሌላ አምላክ የለም ሲሆን ይህም ከአላህ ሌላ ያለውን ማንኛውንም አማልዕክትን ማስካድን ሲሆን ሁለተኛው “ኢለ አላህ” ከ አላህ በስተቀር በማለት አምላክነትን ሙሉ በሙሉ ለአላህ ማረጋገጥን ይነግረናል። ይህንንም አላህ በቁርዓን ውስጥ እንዲህ በማለት ይነግረናል

“ከ አንተ በፊትም እነሆ ከኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢኾን እንጂ ከመልዕክተኛ አንድንም አልላክንም።” (አል-አንቢያ፣ 25)

## 2. ሰላት

አንድ ሙስሊም በቀን አምስት ጊዜ ግዴታ (ፈርድ) የሆኑ ሰላቶች ወቅቱን ጠብቆ መስገድ አለበት። ይህም በቁርዓን ውስጥ እንደተጠቀሰው

“. . .ሰላት በምእመናን ላይ በጊዚያት የተወሰነች ግዴታ ናትና።” ( አል-ኒሳእ፣ 103)

ሰለዚህም ሰውዬው መንገደኛ ካልሆነ በስተቀር ለእያንዳንዱን ሰላት አምስቱን ወቅቱን ጠብቆ እንጂ በተመቸው ሰዓት አንድ ላይ (ጀምዕ) በማድረግ ወደ ፊት ወይም ወደ ኋላ በመውሰድ መስገድ የለበትም።

የሰላት ቅድመ ሁኔታዎች (ሸርጦች) ከዚህ በመቀጠል የተዘረዘሩት ናቸው። እነዚህም፦ ሙስሊም መሆን፣ አእምሮ ጤነኛ መሆን፣ ራስን ማወቅ፣ ትላልቅና ትናንሽ ትጥበቶችን ማድረግ (ከጀናባ ከወሊድና ከወር አበባ ደም መጥራት፣ ውዱእ ማድረግ)፣ ሃፍረተ-ገላን መሸፈን፣ የሰላት ወቅት መግባት፣ፊትን ወደ ቂብላ ማዞር እና ለመስገድ ኒያህ ማድረግ ናቸው።

ሰላትን የሚያበላሹ ነገሮች እንደሚከተሉት ይሆናሉ። ሰላት ውስጥ ሆን ብሎ ማውራት፣ መሳቅ፣ መብላት፣ መጠጣት፣ ሃፈረተ-ገላን መግለጥ፣ በጣም ከቂብላ መዞር፣ ያለማቋረጥ ከመጠን በላይ የሆነ እንቅስቃሴ ማድረግ እና ውዱዕ ማጥፋት ናቸው።

## 3. ዘካ

በእስላም በሶስትኛ ደረጃ የሚገኘው ዘካት ወይም ምፅዋት በመባል ይታወቃል። ከሰው ልጆች መሃል ሀብት ያላቸው በተወሰነ ጊዜ የተወሰነውን የገንዘብ መጠን ከሀብታቸው በግዳጅ መልክ አውጥተው በማህበረሰቡ ውስጥ ላሉ ምስኪኖችና ምፅዋት ለሚገባቸው ሰዎች መስጠት አለባችው ::ዘካ ግደታ የሚሆነው ሃብት ባለው በእያንዳንዱ ሙስሊም ላይ ባለው የገንዘብ ወይም የንብረት መጠን በሐዲስ በተደነገገው መልክ ነው። ይህም

1. ጥሬ ገንዘብ ያላቸው ባለሃብቶች የገንዘባቸው መጠን 85 ግራም ወርቅ ሊገዛ የሚችልበት መጠን ላይ ሲደርስ ሲሆን ከዚህ መጠን በላይ ጥሬ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች በየ ዓመቱ 2.5% ይከፍላሉ:: ለምሳሌ: 20 ሺ.ህ ብር ተቀማ ጭ ያለው ሰው ተቀማ ጩ አመት የሞላው ከሆነ የ 20 ሺ.ህ ብር 2.5% ማለትም 500 ብር ዘካት ይከፈልበታል:: በየ አመቱ እንዲሁ ከጨመረ ይጨምራል ከቀነሰም ከዘካ መነሻ ገደቡ ካልቀነሰ በስተቀር ባለው የገንዘብ መጠን 2.5% ከመቶ ይከፈላል::

2. ወርቅም እንደዚያው ከ 85 ግራም በላይ ከሆነ በየዓመቱ 2.5 % ይከፈላል::

3. ባለ ሸቀጦች ከሆኑ የሸቀጡ ዋጋ በወርቅ ወይም በብር ተተምኖ የግደታው ገደብ ከደረሰ ይከፍላል::

የህፃናትንና የአዕምሮ በሽታ ያለባቸውን ሰዎች በተመለከተ የምሁራኖች አስተያየት ልዩነት ቢኖረውም አብዛኞቹ አሊሞች ትክክለኛው ወኪል ሊያወጣበት ግደታ አለበት የሚለውን አስተያየት ይሰጣሉ::

አብዛኞቹ ዑለማዎች እንደተስማሙበት ለብዙ አመታት ዘካ ሳያወጣ የኖረ ሰው በማዘግየቱ ተጠያቂ ቢሆንም ያለፈውን ሁሉ በመክፈል አላህን (ሱ ወ) ይቅርታ ይጠይቃል::ዘካ ማውጣት ግደታ የሆነበት ሰው በገንዘቡ ምትክ ልብስ ወይም ዕቃ ወይም እህል መስጠት ይችላል ወይ የሚለውን ጥያቄ ኡለማዎች በአንድ ድምፅ እንደማይችልና ቀጥታ ገንዘቡን መስጠት እንዳለበት ተስማምተዋል:: ዘካ የሚከፈላቸው ሰዎች በቁርዓን ውስጥ በሱራ አል-ተውባ 60 ቁጥር ላይ የተዘረዘሩት ናቸው። የዘካ ገንዘብ ለመስጊድና መሰል ኢስላማዊ ስራዎችን መስራት ይቻላል ወይ የሚለውን አብዛኛው የሃዲስ እና የተፍሲር አሊሞች “ፊሰቢሊ.ሏህ” የሚለውን መስጊድ መስራትና መሰል ኢስላማዊ ተግባራትን አያጠቃልልምና ዘካ ለእንደዚህ ስራዎች ሊለጥ አይገባም ሲሉ አንዳንድ አሊሞች ደግሞ “ፊሰቢሊላህ” የሚለው የቁርዓን ቃል የመስጊድና የመድረሳ ግንባታ እና መሰል

Sadr Ethiopia Sisters